# አድዋ ድሌ ተሸከረከረች!

በ ገለታው ዘለቀ

ያምማል እያለ የከተተው
ጉሮ ወሸባው አባተው
የጅግንነት የውኃ ልኬት
የህብር ክንዳችን ጉልበት
የትብብራችን ብርታት
መልህቅ ያገር አንድነት

አድዋ......

ማሳያ ልኬታችንን
የአብሮነት ቃል ኪዳን ውላችንን
የነፃነትን ዋጋ ክብራችንን

አድዋ ክብሬ ናት ኩራቴ
ታሪኬ እምዬ ስስቴ

አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች.....

አንቺ  እርግብ ሆይ ብረሪ
የአድዋ ተራሮችን ድል አብስሪ
የድል ዝማሬን ዘምሪ
ላለም ህዝቦች ሁሉ መስክሪ!

በቅኝ ግዛት ብትር ቆስለው
አንገታቸውን ቀልሰው
የሃዘን በርኖስ ደርበው
ተከፍተውና ቆዝመው
ጉልበታቸው መሬት ጠቅሶ
ከንፈራቸው መሬት ልሶ
ብሶት ሆዳኛቸውን አብሶ
የደም እምባ ሲያለቅሱ
ሃዘን ተጭኗቸው ሲተክዙ
እነሆ ከአፍሪካ ቀንድ ላይ
ከአድዋ ተራሮች ላይ
የምስራች ድምፅ ተሰማ
ነጋልህ ጭቁን ቀናበልማ
መፅናናት ይሁን ለራማ

ያምማል እያለ የከተተው
ጉሮ ወሸባው አባተው

የቅኝ ግዛቱን ጉልበቱ ራደው
የግዛት ዘንጉ  በረደው

በምስራቅ አፍሪቃ ኮከቦች

በኢትዮጵያ ድንቅ ልጆች

እነሆ ......

አዲስ ምእራፍ ተከፈተ
የነፃነት ብርሃን አባተ
ያምማል እያለ የከተተው
ጉሮ  ወሸባው አባተው

አድዋ ድሌ.....

አያ ሆሆ ተሸከረከረች
ሞገሴ አድዋ ዛሬም ከበረች
አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች
ዛሬም ኢትዮጵያ አንድ ናት አለች

አድዋ.....

እናንተ የአድዋ ተራሮች
የአንድነታችን ህያው ምስክሮች
ብርሃናችሁ ዛሬም ይብራ
ይፈንጥቅ የንጋቱ ጮራ
ግለጡ የተፃፈባችሁን
አሳዩ ማተማችሁን

አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች.....

ዘመኑ ሄደ ዘመኑ ጠባ
የአድዋ ፅዋ ከቤቴ ገባ

አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች
የአድዋ ድሌ ዛሬም ከበረች

አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች
ዛሬም ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ 'ያለች!

አያ ሆ ሆ ተሸከረከረች
እኔ ከኢትዮጵያ ወይ ፍንክች አለች!

ድል ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት!

መጋቢት፣ 2013